የአቤቱታ ማመልከቻ በተቻለ መጠን በአማርኛ ቋንቋ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ በእንግሊዝኛ፣ በትግርኛ፣ በኦሮሚኛ ወይም በማንኛውም የክልል የሥራ ቋንቋ መቅረብ ይችላል፡፡ አቤቱታው በተቻለ መጠን በጽሁፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን በቃልም አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአቤቱታ ማመልከቻው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች ማሟላት አለበት፡-

- የአመልካች/ አቤት ባይ/ ስም ከነአያት ድርጅት ከሆነ ሙሉ ስም እና ሙሉ አድራሻ፣
- የተጠሪ ሙሉ ስምና የተሟላ አድራሻ፣
- ጉዳዩ በሌላ ማንኛውም አካል በመታየት ላይ ያለ እንደሆነ ይህኑን መጥቀስ
- ለአቤቱታው መነሻ የሆነና ቅር ያሰኘ ድርጊት ወይም ውሣኔ፤
- አቤቱታ አቅራቢው ለምን ድርጊቱ ወይም ውሣኔው ቅር እንዳሰኘው መጥቀስ
- አቤቱታው የሚቀርበው በወኪል ከሆነ የውክልና ሠነድ ኦሪጅናልና ቅጂ፤
- አቤቱታ አቅራቢው በዕንባ ጠባቂ ተቋም በኩል ምን እንዲደረግለት እንደሚፈልግ መጥቀስ፣
- ለአቤቱታው መነሻ የሆነውን ድርጊት ወይም ውሣኔን የሚመለከቱ ሠነዶች ቅጂዎችን ከአቤቱታው ጋር ማያያዝ፣
- ማንኛውም አቤቱታ ለተቋሙ ከመቅረቡ በፊት በሚመለከተው የአስፈጻሚ አካል የበላይ ኃላፊ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ መሆን አለበት፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ፌዴራላዊና ክልላዊ መንግስት መሥሪያ ቤት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች፣**

- የተሰጠዎት ውሣኔ ፍትሃዊነት ሲጎድለው፣
- ያለበቂ ምክንያት ውሣኔ ሲያዘገዩብዎት፣
- የተሰጡዎት ውሣኔ አድሏዊ ሆኖ ሲያገኙት፣
- ቅሬታዎን ተቀብለው ለማስተናገድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ፣
- መረጃ ሲከለከሉ

ለሕዝብ ዕምባ ጠባቂ ተቋም አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**የመተባበር ግዴታ፣**

ተቋሙ ስልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**ያስታውሱ፡-**

- አቤቱታው በተቻለ መጠን በቂ መረጃና፣
- አቤቱታ የቀረበበት መ/ቤት የበላይ አካል ውሣኔ የሰጠበት ሊሆን ይገባል፡፡

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ቴሌፎን**—0 111580663/51
**ፋክስ**— 0111580638/40
**ፖስታ ሣ.ቁ.** — 2459
**ኢሜል**—ombudsmaneth@ethionet.et

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

◊ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ ቁጥር 211/92 የተቋቋመና በሕግ የተደነገጉ የዜጎች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ፣ ጥራት ፣ ቅልጥፍናና ግልጽነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን የማድረግ ዓላማን ያነገበ ፓርላሜንታዊ ዕንባ ጠባቂ ነው።

◊ ተቋሙ በተለያዩ የስራ ክፍሎች የተዋቀረ ሆኖ ተጠሪነቱ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው።

## ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ስልጣንና ተግባር

◊ አስተዳደራዊ መመሪያዎች፣ ውሣኔዎችና አሠራሮች የዜጎችን ሕገ—መንግሥታዊ መብቶችና ሕጎችን የማይቃረኑ መሆናቸውን መቆጣጠር፣

◊ አስተዳደራዊ ጥፋትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መቀበልና መመርመር፣

◊ የአስፈፃሚ አካል ሥራ በሕግ መሠረት የሚሠራ መሆኑን ማረጋገጥና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈጸሙ ለመከላከል ቁጥጥር ማድረግ፣

◊ አስተዳደራዊ ጥፋት የተፈጸመ መሆኑን ካመነ የመፍትሔ ሀሳብ መሻት፣

◊ አስተዳደራዊ ጥፋቶች የሚሻሻሉበትን ሁኔታ ማጥናትና ሃሣብ ማቅረብ፣

◊ የተሻለ የመንግስት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ሕጎች ወይም አሠራሮች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ፣ አዳዲስ ህጎች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ ማሣሰብ።

## ስልጣንና ተግባሩን ለማሳካት የሚጠቀምባቸው ስልቶች

◊ ሕብረተሰቡ ስለ መልካም አስተዳደር መርሆችና የህግ የበላይነት ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ፣

◊ ሕገ መንግስታዊ መብቱን የተረዳና በደልን የማይሸከም ዜጋ መፍጠር፣

◊ በመንግሥት መ/ቤቶች የሚፈጸም አስተዳደራዊ በደልን አስመልክቶ የሚነሳ ቅሬታ እዚያው ባለበት እንዲፈታ ተቋማቱ ስልት እንዲቀይሱ ማበረታታትና ማገዝ፣

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ዕምባ ጠባቂ ተቋም አቤቱታዎችን እንዴት ይመረምራል?

◊ ተቋሙ በአመልካቾች ከሚቀርቡ አቤቱታዎች በተጨማሪ በአስፈጻሚው አካል የሕግ መተላለፍ ወይም የአስተዳደራዊ ጥፋት ተፈጽሟል ብሎ ካመነ በራሱ ተነሳሽነት ምርመራ ያካሄዳል።

◊ ተቋሙ ይህን ዓይነት ምርመራ ሲያካሂድ የሚመለከተውን የአስፈፃሚ አካል በመጥራት ሊጠይቅ፤ እንደዚሁም ሠነድና ሌሎች ማስረጃዎችእንዲያቀርብ ሊያደርግ ይችላል።

◊ ተቋሙ ምርመራ ካካሄደ በኋላ አስተዳደራዊ ጥፋት ተፈጽሟል ወይም ሕግ ተጥሷል ብሎ ካመነ ለዚህ አስተዳደራዊ ጥፋት ምክንያት የሆነ ድርጊት ወይም አሠራር እንዲቆም ወይም ለጥፋቱ ምክንያት የሆነው መመሪያ ተፈፃሚነቱ ቀሪ እንዲሆንና የተፈጸመው የአስተዳደር ጥፋት እንዲታረም ወይም ተገቢ የሆነ ማንኛውም ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

◊ ተቋሙ አቤቱታዎችን ተቀብሎ የሚመረምረው ያለምንም ክፍያ ነው።

## ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም መቅረብ የሚችሉ አቤቶታዎች

◊ የፌዴራል መንግስት ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ኮሚሽኖች፣ ኤጀንሲዎች፣ ኢንስቲትዩቶች፣ ድርጅቶችና የነዚህ አካላት ኃላፊዎች የሚያሣልፉት ውሣኔዎች፣ የሚያወጡት መመሪያዎችና የሚወስዱት እርምጃዎችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች፣

◊ የክልል መንግሥታት (አዲስ አበባና ድሬዳዋን ጨምሮ) አስፈጻሚ አካላትና በነሱ ሥር የሚገኙ ተቋሞችና ኃላፊዎች የሚያስተላልፉት ውሣኔ፣ የሚያወጡት መመሪያና የሚወስዱት እርምጃን የሚመለከቱ አቤቱታዎች፣

◊ የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍ/ቤቶች፣ የአገር መከላከያና ደህንነት፣ የፌዴራልም ሆነ የክልል ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ያሉ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፎች/ ጠቅላላ አገልገሎት ክፍሎች/ የሚያሳልፉትን ውሣኔዎች፣ የሚያወጡትን መመሪያዎችና የሚወስዱትን እርምጃዎች የሚመለከቱ አቤቱታዎች ናቸው።

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ዕምባ ጠባቂ ተቋም የማያስተናግዳቸው አቤቱታዎች

◊ በማናቸውም ደረጃ በፌዴራልም ሆነ በክልል ፍ/ቤ/ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች፣

◊ የፌዴራልም ሆነ የክልል ምክር ቤቶች /ፓርላማዎች/ በሕግ አውጪነታቸው የሚያሳልፉት ውሣኔዎችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች፤

◊ በዋና ኢዲተር መ/ቤት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች፣

◊ በጸጥታ ኃይሎችና በመከላከያ ሠራዊት ክፍሎች የሚሰጡ የጸጥታ ወይም የሀገር መከላከል ጉዳዮችን በሚመለከት ከሚሰጡ ውሣኔዎች ጋር የተያያዙ አቤቱታዎች፣

◊ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን(NGO$_S$)፣ ኃይማኖታዊ ተቋሞችን የሚመለከቱና ከግለሰቦች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው።

## አቤቱታ እንዴት ማቅረብ ይቻላል?

የአቤቱታ ማመልከቻ በመፃፍ ወይም ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማቅረብ ይችላሉ። ቅጹን ከሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ቢሮ ወይም ከዌብሳይት ማግኘት ይቻላል።